ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

Coalition for Unity and Democracy Party
(Kinijit)

## *ዜና ነክ መግለጫ፤ News Release:*
## በኢትየጵያ የህሊና እስረኞች ላይ የታሰበውን የካቲት 12 1999ቱን የፍትህ ቧልት አስመልክቶ::
## *In relation to the coming Feb 19 2007 sham trial of prisoners of conscience in Ethiopia:*

**የከቲት 2 1999… ቁጥር 1**
February 9, 2007… NO **1**

***ይህ ዜና ነክ መግለጫ የሚዘጋጀው በቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ ነው:: አላማው ወያኔ/ኢህአዴግ በግፍና በሃሰት ባሰራቸው የቅንጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የሰብአዊና የዜጎች መብቶች ተሟጋቾች ላይ የካቲት 12 ቀን በፍትህ ስም ሊያስተላልፈው ያቀደውን እኩይ ውሳኔ ለማሰቆም በሃገር ቤትና በአለም ዙሪያ እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ በዜና መልክ ማቅረብ ነው::**

***በፍትህ ስም ሊፈጸም የታሰበውን የወያኔ ግፈኛ ደባ ለመቃወም፣ ይህ ደባ ለራሱ ለወያኔም የማይበጀው መሆኑን ለማስጠንቀቅና ለመምከር፣ ወያኔ ታዛዥ ሆኖ ስላገኙት ብቻ በጊዚያዊ መሳሪያነት ለመጠቀም በማሰብ የሚፈጽመውን ግፈኛ ድርጊት አይናቸውን ጨፍነው ለማለፍ የሚገፈልጉትን የውጭ መንግስታት ስህተት ለማሳየት በሰላማዊ ሰልፍ፣ በሻማ ማብራት በዲፕሎማሲና በሎቢ መልኩ የሚደረገው እንቅስቃሴ ቀጥሏል::**

***በሐገራቸው የነጻነት፣ የፍትህ፣ የህይወትና ስራ ሰርቶ የመኖር ዋስትና በማጣታቸው በአለም ዙሪያ እንደ አሸዋ መበተን እጣቸው የሆነው ኢትዮጵያውያን ዛሬም እንደ ትናንቶቹ ሐገር ወዳድ ቀደምቶቻቸው «ኢትዮጵያችን አንችን ብንረሳ የሚረሳ ይርሳን» እያሉ ናቸው:: በተከታታይ መንግስታት ብዙ በደልና ግፍ እየተፈጸመባቸው ሐገርን ጥለው የስደትን ሕይወት እንዲመርጡ ቢገደዱም፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ምሬታቸው በግፈኛ መሪዎች እንጂ፣ በሐገራቸው ላይ እንዳልሆነ ሐገራቸውና ወገናቸው ችግር ላይ በወደቁ ቁጥር የቻሉትን በማድረግ ድምጻቸውን ሲያሰሙ ኖረዋል:: ኑሮውን በውጭ ሐገር ካደረገ ከየትኛውም የሌላ ሐገር ዜጋ ጋር ሲነጻጸር፣ እንደ ኢትዮጵያዊ ሐገሩን በሚመለከት የሚቃጠል ዜጋ ማግኘት አይቻልም:: ይህ ስሜት ከመቼውም የበለጠ እየጨመረና እየጋለ የሚሄድ ለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎች እያየን ነው:: በአንድ አንድ ሐገሮች ሰዎች በሽዎች ከእዛም በላይ በመቶ ሽዎች በግፍ ሲረግፉ ከሀገር ውጭ የሚገኙ ዜጎቻቸው፣ በአለም ዙሪያ ቀርቶ በአንድ ሐገር ውስጥ እንኳን ድምጻቸውን እንደማያሰሙ እናውቃለን:: ኢትየጵያውያን ግን በአለም ላይ በሚገኙት ክፍለ አለማት በሙሉ በአንድ ግዜ፣ ከሰላሳ በሚበልጡ ሐገሮችና ክፈለ ሐገሮች ውስጥ ተነስተው የተቃውሞ ድምጻቸውን አሰምተዋል:: ይህ የሐገር ተቆርቋሪነት ባህል ኢትየጵያችን ያለአግባብ ስትደፈር ወይም ሕዝባችን በረሃብ ሲጠቃ ብቻ የሚቀሰቀስ አይደለም:: በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ የሕዝብን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለማስከበር የሐገሪቱ ሕዝብ ብቃቱም ፍላጎቱም እንዳለው ያረጋገጠበትን ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት ግንባታ ደንቃራዎች ለመጥረግ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በማሰማት ላይ ናቸው:: ወያኔ/ኢህአዴግ በሰኔ 1997ና በጥቅምት 1998 ወራት የሕዝብን ድምጽ አጭበርብሮ ስልጣን ላይ ለመቆየት ሲል በሕዝባችን ላይ ያካሄደውን ግፈኛና ዘረኛ ጭፍጨፋ፣ ለአለም ሕዝብ በአለም ዙሪያ አጋልጠዋል:: የወያኔ የዴሞክራሲ አስመሳይነት ካባ ወልቆ፣ የዘረኛነትና የአምባገነንት**

እርቃኑ እንዲጋለጥ በተደረገው ጥረት፣ ሐገር ወዳዱ ኢትዮጵያዊ ያደረገው አለም አቀፋዊ የተቀነባበረ እንቅስቃሴ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

*ሰሞኑን ደግሞ የካቲት 12 1999 ከመድረሱ በፊት በአለም ዙሪያ የሚገኙ ኢትየጵያውያን «የሃሰት ክስ ያብቃ፣ የቅንጅት መሪዎች ጋዜጠኞችና የሰቪልና የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪዎች ባስቸኳይ ይፈቱ፣ ቅድሚያ ለእርቅ ለመቻቻል በጋራ ለሚገነባ የዴሞክራሲ ሥርአት ይሰጥ» በሚል ቀና ትልም ዙሪያ የተቀነባበረና የተደራጀ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ናቸው። የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች፣ ከቅንጅት አለምአቀፍ የፖለቲካ አመራርና በየሐገሩ ከሚገኙ የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር በመመካከር የተቃውሞ ሰልፍና የዲፕሎማሲ ሥራ ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል። በአንዳንድ ቦታዎች እንቅስቃሴው ተጀምሯል።

*በያዝነው ሳምንት ውስጥ በአፍሪካ፣ በአውስትራሊያ፣ በካናዳ፣ በአውሮፓና በሰሜን አሜሪካ በሚቀጥለው ሳምንት ለሚደረገው ሰፊ የሰላማዊ ሰልፍ እንቅስቃሴ የተደረገውን ዝግጅት የሚገመግሙ ስብሰባዎች ተደርገዋል። በአንዳንድ ሐገሮች፣ በብሪታንያ በስዊድን ለፖለቲካ ድርጅቶች ደጋፊዎች ገለጻ ተደርጓል። በሰሜን አሜሪካ በሚገኙ ክፍለሃገሮች፣ ባለፈው ሳምንት የታሰሩት እንዲፈቱ፣ ሰላምና እርቅ እንዲወርድ ጸሎት አንዲደረግ በተደረገው ተማጽእኖ የሃይማኖት ተቋማትና ምእመናን በጋራና በተናጠል ፈጣሪያቸውን ተማልደዋል።

ከእዚህ በተጨማሪ ከአለም ዙሪያ የደረሰን ሪፖርት እንደሚያሳየን፣ የሰላማዊ ሰልፍ እንቅስቃሴና የሻማ ማብራት ተግባር ዛሬ በእንግሊዝ ሐገር በጠቅላይ ሚኒስተር ቶኒ ብሌየር መኖሪያና መስርያ ቤት ፊት ለፊት ይደረጋል። ይህ የዛሬው የሻማ ማብራት ሰልፍ በሚቀጥለው ሳምንት ፌብሯሪ 16  በኢትዮጵያ ኤምባሲ ፊት ለፊት የሚደረገው ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ አካል ነው። እንደሚታወሰው ጠቅላይ ሚኒስቴር ቶኒ ብሌየር የዛሬ ሁለት አመት መለስ ዜናዊ አስጠግተው የመልካም አስተዳደር ምሳሌ ይሆናል ብለው ሲያሞካሹት እንደነበር  ይታወቃል። ነገር ግን ዛሬ በምድር ላይ አይኑን ማየት ከማይፈልጉት መሪ አንዱ መለስ ዜናዊ ለመሆን በቅቷል። ጠቅላይ ሚኒስቴር ቶኒ ብሌየር «መለስ ዜናዊ በኢትየጵያ የዲሞክራሲ ወገኖችንን በግፍ በመጨፍጨፍና በማሰር በወሰዳቸው እርምጃዎች በአለም ፊት እንዳፍር አድረጎኛል፣ የጣልኩበትን አመኔታ የካደ አደራ የበላ ነው» የሚል ቁጭት እንዳላቸው ይታወቃል። በመለስ ዜናዊና በእንግሊዝ መንግስት መካካል የቀረ ግንኙነት ቢኖር፣ የእንግሊዝ መንግስት እንደ አሜሪካ አቻው በጸረ ሽብር እንቅስቃሴ እስከአንገቱ የተነከረ በመሆኑና የአሜሪካንን መንግስት ስሜት ለመጠበቅ የእንግሊዝ መንግስት በሚያሳየው ትእግስት ላይ የቆመ ነው። እራሱን የጸረ ሽብርተኛ ወዳጅ አድርጎ ለአሜሪካኖች ያቀረበውን መለስ ዜናዊን በማስቀየም አሜሪካኖችን ላለማስከፋት ሲል የእንግሊዝ መንግስት በቀዝቃዛ ስሜት የመለስን መንግስት እያየ ይገኛል።

*በሚቀጥለው ሳምንት የሚደረጉት የመጀመሪያዎቹ ሁለት እንቅስቃሴዎች በደቡብ አፍሪካ ይከናወናሉ። በፌብሯሪ 12 የደቡብ አፍሪካ የኢትዮጵያ ስደተኞች ማህበረሰብና የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት በጋራ በጠሩት ሰልፍ ላይ በፕሪቶሪያ ውስጥ ኢትዬጵያዊያን  ሰልፍ ያደርጋሉ። ፌብሯሪ 14 በሁለቱም ቡድኖች የተጠራው ሰልፍ በጆሃንስበርግ በርካታ ሕዝብ የሚሳተፍበትና፣ ለእዚህንም ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑ ታውቋል።

እስካሁን ባለን መረጃ መሰረት በፌብሯሪ 15ና 16 የሚደረገው አለም አቀፍ ትእይንተ ሕዝብና የሻማ ማብራት፣በአምስት ክፍለአለማት የ12ና የ14ቱን የደቡብ አፍሪካ ዝግጅት ጨምሮ በአውስትራሊያ ካምቤራ ከተማ ላይ፣ በአውሮፓ በአሜሪካና በካናዳ የሚካሄድ ሲሆን፤ በአውሮፓ በስምንት ትላልቅ የምእራብ አውሮፓ ሐገራት ከተሞች ይደረጋል። በብረስልስ፣ በቪየና በለንደን በዴንሃግ፣ በርሊን፣ በርን፣ ኦስሎና ሰቶከሆልም ከተሞች ላይ ይደረጋል። በሰሜን አሜሪካ ዋናው ሰልፍ በፌብሯሪ 15 በዋሽንግተን ዲሲ የሚደረግ ቢሆንም በተለያዩ የአሜሪካ ክፈለ ሃገሮች በቦስተን፣ በሎስአንጄለስ፣ በአትላንታ፣ በዴንቨር፣ በሚኔሶታ፣ በፊኒክስና በሌሎችም ከተሞች ሰልፉና ሻማ ማብራቱ  እንደሚደረግ ታወቋል። በካናዳም በቫንኩቨር፣ በካልጋሪ ፣በዊኒፔግና በቶሮንቶ/ኦቶዋ ይደረጋል። በአለም ዙሪያ የሚደረገውን ሠልፍ ዝርዝር መረጃ ማየት ከፈለጉ፣ በተለይ ሰአትና ቦታን በሚመለከት፣ የቅንጀትን ኦፊሴላዊ ድረ-ገጽ www.kinjitethiopia.org እንዲጎብኙ ተጋብዘዋል።

*በሌላ በኩል ደግሞ በዲፕሎማሲ መስኩ በመሰራት ላይ ያለውን ስራ በሚመለከት የደረሰን ዜና እንደሚያሳየው፣ በአለም ዙሪያ የሚደረገው ዲፕሎማሲያዊ ግፊት ተጠናክሮ ቀጥሏል:: ለመንግስት መሪዎች፣ ለፓርላማና ለኮንግረስ ተመራጮች፣ ለሴቶች ለሰብአዊ መብት ድርጅቶች፣ ለሃይማኖት ተቋማት፣ በአለም ላይ ለሚገኙ የታላላቅ ከተሞች ከንቲባዎች፣ ለሰራተኛ፣ ለመምህራን፣ ለጋዜጠኞች ማሕበራትና መሪዎች በተደራጀ መንገድ ከማእከል የተዘጋጁት ደብዳቤዎች እንዲሰራጩ ተደርጓል:: አላማው በየሐገሩ የሚገኙ ታላላቅ ተቋማት በኢትዮጵያ የሚካሄደውን አሰቃቂ የሰብአዊና የሲቪል መብቶች ረገጣ እንዲገነዘቡ በማድርግ በመንግስታት ላይ ተጽእና እዲያደርጉ ለማድረግ ነው:: የዲፕሎማሲ ስራው እነዚህን ተጽእኖ ማድርግ የሚችሉ ተቋማት ሳያሳትፍ፣ የየሐገሩ መንግስታት በኢትዮጵያ ላይ የያዙትን  የተሳሳቱ ፖሊሲዎች ማስቀየር እንደማይቻል በማመን ነው::

*ከእዚሁ የዲፕሎማሲያዊ እንቅስቀሴ ጋር ተያይዞ በአውሮፓ ውስጥ በላፉት ጥቂት ሳምንታት በኖርዌይ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅት የተጀመረውና አጥጋቢ ፍንጮች የታዩበትን የተለያዩ መንግስታትንና የተቋማት ባላስልጣናትን በአካል ማግኘትና የማነጋገሩ እንቅስቃሴ በአውሮፓ ተጠናክሮ ይቀጥላል:: በያዝነው ሳምንት ሎንዶን ላይ በኢትዮጵያ የሚካሄደውንና ሰሞኑን ተጠናክሮ የቀጠለውን የጅምላ እስራትና የማፍያ መልክ ያለው ግድያ፣ እንዲሁም በመጭው ፌብሯሪ 19 ወያኔ ሊወስድ ያሰበውን እኩይ እርመጃ በሚመለከት ከአምነስቲ አለመአቀፍ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጓል:: የፌብሯሪ 19 የፍርድ ቤት ቧልት የወደፊቱን የኢትዮጵያ እጣ በተለይ በሰላምና በመረጋጋት ጉዳይ ሊያስከትለው የሚቸለውን አደጋ ቅንጅት እንዴት በስጋት እንደሚያየው ገለጻ ተደርጓል:: ይህ የብይን ውሳኔ ወያኔ/ኢህአዴግ እንደሚያስበው እስረኞቹን በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ ወንጀለኛ አድርጎ የሚፈጸም ከሆነ በሃገሪቱ ውስጥ ሊከሰት የሚቸለው አደጋ በሰብአዊ መብት  ጥሰት በኩል የሚኖረውን አስፈሪ መዘዝ ለማስረዳት ተሞክሯል:: በሚቀጥለው ሳምንት መጀመሪያ ገደማ የተለያዩ መንግስታት ባለስልጣናት በማግኘት የሚደረገው የሎቢ ስራ በመቀጠል ከጀርመንና ከእንግለዝ የውጭ ግንኙነት ባለስልጣናት ጋር የአካለዊ ግንኙነት ለማድረግ ቀጠሮ ተይዟል::

*በመጨረሻም ይህ በውጭ ሐገር የሚደረገው የታቃውሞ፣ የማስጠንቀቂያና የተማጽኖ እንቅስቃሴ በሃገር ውስጥ እንዴት መደረግ እንደሚገባው ዝርዝር መመሪያ በሚቀጥለው ሳምንት መጀመሪያ በቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ ተዘጋጅቶ በተለያዩ መንገዶች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚቀርብ መሆኑ ከቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ተገልጧል:: ይህ ጥሪ የኢትዮጵያ  ሕዝብን ድምጽ አናሰርቅም በማለት ለሕዝብ የገቡትን ቃል ላለማጠፍና ሕዝብም «ወያኔ በማጭበርበር በጉልበት በያዘው ፓርላማ ውስጥ አትግቡ» ያላቸውን መመሪያ በመቀበል እራሳቸውን ለሞት፣ ለእስራትና ለእንግልት የዳረጉትን መሪዎቹን፣ አንደበት ሆነው ያገለገሉትን ጋዜጠኞችን፣ ሕዝብ ለመብቱ እንዲቆም የቀሰቀሱትን የሰብአዊ መብት ጠበቆቹን ለመታደግ ከእስር እንዲፈቱ፣ ስቃይ እንዲያበቃ እርቅና ሰላም በሐገራችን እንዲወርድ ለማድረግ፣ በእብሪት መጓዙ ለአለፉት ፈለጭ ቆራጮችም እንዳልበጀ፣ ለዘመኑ አምባገነኖች ለማስታወስ የሚደረግ እንቅስቃሴን የሚያበረታታ ጥሪ ይሆናል:: ዝርዝሩ በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ይቀርባል::

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ